# ወቅታዊ ታላቅ ስብሰባ በአትላንታ

ህዝባችን መብትና ሥልጣኑን በኢሕአዴግ ተነጥቆ ከፍተኛ በደልና ግፍ እየተፈፀመበት መሆኑ የሚታወቅ ነው። ሃላፊነት የማይሰማቸው ጠመንጃ ነካሽ ገዥዎቻችን ህዝባችንን በተለያዩ ጦርነቶች ውስጥ እያስገቡ ሲያስጨርሱ ቆይተዋል። አሁም እያደረጉት ነው። ከዚህም አልፈው በህዝባችን ውስጥ መለያየት እንዲፈጠር አንዱን ከአንዱ ጋር በተንኮል ሲያጋጩ ቆይተዋል። ባለፉት አመታትና ወራት በተለያዩ ሃይማኖቶች አማኞችና ቋንቋ ታናጋሪዎች መካካል የተከሰቱትን ግጭቶች ለዚሁ መሰሪ ተንኮል በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው። የአገራችንም ሉአላዊነት በከፍተኛ አደጋ ላይ ተንጠልጥሎ እንደሆነ የምንገነዘበው ነው። ይህን አሳዛኝ ታሪክ መለወጥ የምንችለው ኢትዮጵያውያን በመከባበርና በመተባበር መታገል ስንችል ነው። ክዚህ አንፃር በትግሉ ውስጥ ያሉ ድርጅቶች ማለትም የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃ አውጭ ግንባር፣ የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር፣ ቅንጅት ለዴሞክራሲና ለአንድነት፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ሕብረት፣ የሃይማኖት መሪዎችና የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች በመጋበዝ ሰፊ ውይይት ለማድረግ ዝግጅት አድርገናል።

በዚህ ቀን በኢትዮጵያ እስላሞችና ክርስቲያኖች ለረጅም ዘመን ተስማምተው እንዲኖሩ አስተዋፅዖ ያደረገውን የነብዩ መሐመድን መልእክት የሚያሳይ አንድ ፊልም ይታያል። ከዚያም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት ይደረጋል። ስለዚህ የህዝባችንን መብት ለማስከበር የአገራችንን ሉአላዊነት ለማስጠበቅ ለመመካከር በሚደረገው በዚህ ስብሰባ ሰአቱን በማክበር እንድትገኙልን የክበረ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የሕብረት ድጋፍ አዘጋጅ ኮሚቴ በአትላንታ

ቀን: January 13, 2007

ሰአት 12:00pm ፊልሙ ይጀምራል።
በመቀጠልም እንግዶች ወደ መድረክ በመቅረብ አጠር አጠር ያለ ንግግር ያደርጉና ውይይቱ ይከተላል።

ቦታ: Decatur Public Library Center
215 Sycamore Street
Decatur Ga. 30030